# የወዳጄ የአህመድ ጥያቄ

አላህ ኢየሱስ ክርስቶስን መስዋዕት ሳያደርግ ሊያድነን
አይችልም ነበር?

በሳሂህ ኢማን

ለ………………………………………………….

ወዳጄ የህክምና ተማሪ ነው፡፡ የተዋወቅነው ይህንን ጽሑፍ ለመጻፍ ከተቀመጥኩበት ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ነው፡፡ ከወዳጄ ጋር ስንገናኝ ስለ እምነታችን እንድናወራ በሚጋብዝ ሁኔታ ውስጥ ነበርን፡፡ እናም እምነታችንን በተመለከተ ስንወያይ ሳለ፣ በሃይማኖት ጥላ ውስጥ የሆነ እምነት ግቡ ጀነት መግባት ነውና ወደዛው ስለ መግቢያ መንገዶች መነጋገር ጀመርን፤ በዚህ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፡- "አላህ ኢየሱስ ክርስቶስን መስዋዕት ሳያደርግ ሊያድነን አይችልም ነበር?" ለዚህ ጥያቄው እኔም ምላሹን ሰጥቸው ነበር፡፡ ሆኖም ከዚያ በኋላ የዚህ ሰው ጥያቄ የስንት ሙስሊሞች ጥያቄ ይሆን? ብዬ እራሴን መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ ምናልባት የበርካቶች ሊሆን ይችላል፤ ከነዛም እርስዎ አንዱ ይሆኑ? ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለማንኛውም ይህ የወዳጄ ጥያቄ በሕሊናቸው ውስጥ እረፍት የነሳቸው ሁሉ፣ የዘላለም መንገዳቸውን ለመመርመር እድሉን እንዲያገኙ፣ የተጠየኩትን ጥያቄና ለዛም የሰጠሁትን ምላሽ ላስነብባቸው ቆረጥኩ፤ ብዕሬንም ከወረቀት አዋደድኩ፡፡ ውድ አንባቢ፤ ለወዳጄ ለአህመድ እንዲህ በማለት ነበር የመለስኩለት፡-

ወንድሜ አህመድ ሆይ እስኪ ለምሳሌ ምን ቢያደርግ ብለህ አሰብክ? ትንሽ ከጠበቅኩት በኋላ ምናልባት ሙስሊም ስለሆንክ የእስልምና ሃይማኖትን ሕግጋት እንድንጠብቅ፤ የነቢዩንም ሱናዎች እንድንከተል በማድረግ? በአማራጭነት የሚታየው እርሱ ስለሆነ ብዬ ነው፡፡ አዎን ከሆነ መልስህ፣ እኔም እስኪ የተወሰኑ ጥያቄዎች ልጠይቅህ፡-

- አንተ የምታስባቸውን እነዛን የእስልምና ሃይማኖት ሕግጋት በመጠበቅና የነቢዩን ሱናዎች በመከተል አላህ ወደ አዘጋጀው ጀነት ለመግባትህ ምን ያክል እርግጠኛ ነህ?
- አላህ የአደምን ልጆች ግማሹን ለጀነት ግማሹንም ለጀሃነም እንደፈጠራቸው ነቢዩ ሙሐመድ በሐዲሳቸውና በቁርአን ተናግረዋል፤ ታዲያ ሕግጋቱን መፈጸም አለመፈጸም በአንተ ፍጻሜ የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል? ደግሞስ ከሁለቱ አንተ ከየትኛው ወገን ነህ? ከየትኛው ወገን እንደሆንክስ እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? ከየትኛው ወገን ለመሆንስ ትሠራለህ? የነቢዩን ሐዶሶችና የቁርአኑን አንቀጾች በሚቀጥሉት ገጾች ላይ ከበርካታዎቹ በጣም ጥቂቱን ታገኛቸዋለህ፡፡
- ሕግ በባህሪው የሰውን በትዕዛዛቱ ፍጹም ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል፡፡ ምናልባት በርካታ ሕግጋቶችን ጠብቀህ ድንገት አንዱን ብትተላለፍ በዛ ከመጠየቅና ከመቀጣት አታመልጥም፡፡ ታዲያ አንተ አሁን በእስልምና በተሰጡት ሕግጋቶች ፍጹም ሆነህ እራስህን አግኝተኸዋል? በአላህ ፊትስ ፍጹም የሚሆን ሰው ይኖራል ብለህ ታስባለህ? የአላህ መልእክተኛ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ነቢዩ ሙሐመድም ስለእራሳቸው ፍጹም ሰው ነኝ፤ የአላህን ሕግጋት በትክክል ፈጽሜአለሁ፤ ጀነት ለመግባቴም ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለኝም፣ በማለት አንድም ቦታ

አልተናገሩም፡፡ ይልቁን ስለ ኃጢአታቸው በቀን ሰባ ጊዜ ንስሃ ይገቡ እንደነበር በሐዲሳቸው ተዘግቧል፡፡

- ምልባት ሁሌ እንደሚባለው፣ አላህ መሐሪ ስለሆነ በምህረቱ ጀነት ያስገባኛል፤ ትለኝ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሕግ በባህሪው ፍጹም ሆኖ ያልተገኘን ሰው መቅጣት እንጂ መማር አያውቅም፤ አላህ ለነቢዩ የሰጠው ደግሞ ሕግ ነው፡፡ እንደ እስልምና አስተምህሮ የሰው ፍጻሜ ከመወለዱ ወይንም ከመፈጠሩ በፊት፣ በአላህ የተወሰነ ስለሆነ ውሳኔውን ሊያጥፈው አይቻልም፡፡ ሊያጥፈው ይችላል ከተባለ ከማንነቱ ጋር ይጣረሳል፤ አላህ በባህሪው እራሱን ሊጣረስ የሚችል አምላክ አይደለም፡፡ ታዲያ ሌላ ምን ቢያደርግ ከዘለአለም ሞት መዳን ይቻላል ብለህ ታስባለህ?
- ሌላው እነዚህ በነቢዩ ሙሐመድ በኩል የተላለፉት የእስልምና ሃይማኖት ሕግጋቶች ኃጢአትንና ሰውን በማለያየት ጀነት የመግባት ዋስትናን ያረጋግጣሉ ብለህ ታምናለህ? ከአላህ የተሰጡ ሕግጋቶች ለመሆናቸውስ ምን ያክል እርግጠኛ ነህ? በምን ገምግመህቸው እርግጠኛ ሆንክ? የእስልምናው ሕግጋትና የእምነቱ ስርአቶች ከትንሽ ማሻሻያ በስተቀር ሁሉም ማለት ይቻላል፣ በጣኦት አምልኮው ዘመን ከቁሬይሽና ከአረቢያ ጣኦት አምላኪዎች የሃይማኖት ሕግጋትና የጣኦት አምልኮ ስርአቶች ጋር፣ ፍጹም አንድነትና ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡
- ከእስልምና ሃይማኖት ሕግጋትና ከእምነቱ ስርአት ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት የነበረው የቁሬይሾቹና የአረብ ጣኦት አምላኪዎች ሃይማኖት፣ በነቢዩ ሙሐመድ ከተወገዘና ሰይጣናዊ ነበር ከተባለ፣ ጀነት ለመግባት ዋስትና የማይሆን ከሆነ፣ ያን የነቀፈ ግን በሥራው ፍጹም የሚመሳሰለው እስልምና፣ ከአላህ ነው ሊባል ጀነት ለመግባትም አስተማማኝ ዋስትና ያለው ትክክለኛ መንገድ እንዴት ሊሆን ይችላል?

እስኪ የሚከተሉትን የቁርአን አንቀጾችና የነቢዩን ሐዲሳት አንብባቸውና ነገሩን ለመገምገም ሞክር፡-

**ሱረቱል አል-አንአም /የቤት እንስሳዎች ምእራፍ/ 6 ፡ 125**

አላህም <u>ሊመራው የሚሻውን ሰው</u> ደረቱን (ልቡን) ለኢስላም ይከፍትለታል፡፡ <u>ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው</u> ደረቱን ጠባብ ቸጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል፡፡ እንደዚሁ <u>አላህ በእነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል፡፡</u>

فَمَن يُرِدِ اللَّهُ أَن يَهْدِيَهُ يَشْرَحْ صَدْرَهُ لِلْإِسْلَامِ ۖ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُ يَجْعَلْ صَدْرَهُ ضَيِّقًا حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي السَّمَاءِ ۚ كَذَٰلِكَ يَجْعَلُ اللَّهُ الرِّجْسَ عَلَى الَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ

**ሱረቱል አል-አእራፍ /የአዕራፍ ምዕራፍ/ 7 ፡ 178-179**

***<u>አላህ የሚያቀናው ሰው ቅን እርሱ ነው፡፡ የሚያጠመውም ሰው እነዚያ ከሳሪዎቹ እነሱ ናቸው</u>፡፡ ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን ለገሀነም በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ለእነርሱ በርሳቸው የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው፡፡ ለእነሱም በሳቸው የማያዩባቸው ዓይኖች አሉዋቸው፡፡ ለእነሱም በሳቸው የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሉዋቸው፡፡ እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው፡፡ ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፡፡ እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ናቸው፤***

مَن يَهْدِ اللَّهُ فَهُوَ الْمُهْتَدِي ۖ وَمَن يُضْلِلْ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الْخَاسِرُونَوَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ الْجِنِّ وَالْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ آذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَا ۚ أُولَٰئِكَ كَالْأَنْعَامِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ أُولَٰئِكَ هُمُ الْغَافِلُونَ

**ሱረቱል ሁድ /የሁድ ምዕራፍ/ 11 ፡ 118-119**

***<u>ጌታህም በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ሕዝብ ባደረጋቸው ነበር፡፡ የተለያዩም ከመሆን አይወገዱም፡፡ ጌታህ ያዘነለት ብቻ ሲቀር፤ (ከመለያየት አይወገዱም)፡፡ ለዚሁም ፈጠራቸው፡፡</u> የጌታህም ቃል ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች ከሁሉም በእርግጥ እሞላታለሁ በማለት ተፈጸመች፡፡***

وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَجَعَلَ النَّاسَ أُمَّةً وَاحِدَةً ۖ وَلَا يَزَالُونَ مُخْتَلِفِينَإِلَّا مَن رَّحِمَ رَبُّكَ ۚ وَلِذَٰلِكَ خَلَقَهُمْ ۗ وَتَمَّتْ كَلِمَةُ رَبِّكَ لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنَ الْجِنَّةِ وَالنَّاسِ أَجْمَعِينَ

**ሱረቱል ዩኑስ /የዩኑስ ምዕራፍ/ 10 ፡ 99-100**

***<u>ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን? ለማንኛዋም ነፍስ በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ</u>***

ልታምን (ችሎታ) የላትም፡፡ (አላህ ለከፊሎቹ እምነትን ይሻል)፡፡ በእነዚያም በማያውቁት ላይ ርክሰትን ያደርጋል፡፡

وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَن فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا ۚ أَفَأَنتَ تُكْرِهُ النَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُوا مُؤْمِنِينَوَمَا كَانَ لِنَفْسٍ أَن تُؤْمِنَ إِلَّا بِإِذْنِ اللَّهِ ۚ وَيَجْعَلُ الرِّجْسَ عَلَى الَّذِينَ لَا يَعْقِلُونَ

**ሱረቱል አል-ነኽል 16 ፡ 93**

አላህም በሻ ኖሮ አንዲት ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን የሚሻውን ሰው ያጠማል፡፡ የሚሻውንም ሰው ያቀናል፡፡ ትሠሩት ከነበራችሁትም ሁሉ በእርግጥ ትጠየቃላችሁ፡፡

وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَجَعَلَكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَٰكِن يُضِلُّ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي مَن يَشَاءُ ۚ وَلَتُسْأَلُنَّ عَمَّا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ

**ሱረቱል አል-ኢስራ 17 ፡ 83**

በሰውም ላይ ጸጋችንን በለገስን ጊዜ (ከምስጋና) ይዞራል፡፡ ጎኑንም (ከእውነት) ያርቃል፡፡ ችግርም በነካው ጊዜ ተስፋ ቆራጭ ይኾናል፡፡

وَإِذَا أَنْعَمْنَا عَلَى الْإِنسَانِ أَعْرَضَ وَنَأَىٰ بِجَانِبِهِ ۖ وَإِذَا مَسَّهُ الشَّرُّ كَانَ يَئُوسًا

**ሱረቱል አስ-ሳጂዳ 32 ፡ 13**

በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር፡፡ ግን ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ እሞላለሁ ማለት ቃሉ ከእኔ ተረጋግጧል፡፡

وَلَوْ شِئْنَا لَآتَيْنَا كُلَّ نَفْسٍ هُدَاهَا وَلَٰكِنْ حَقَّ الْقَوْلُ مِنِّي لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنَ الْجِنَّةِ وَالنَّاسِ أَجْمَعِينَ

እንግዲህ ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ በእነዚህ የቁርአኑ አንቀጾች በኩል እየነገረን ያለው የሰውን ልጆች አማኝም የማያምኑ ያደረጋቸው፣ በሃይማኖትና በእምነት እንዳይመሳሰሉ፣ ግማሹ እንዲገዛለት ሌላው ደግሞ

እንዳይገዛለት ያደረገና ሁሉን የፈጠረ እራሱ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአንተ ሕይወት ውስጥ ለሚፈጸመው የኃጢአትም ሆነ የጽድቅ ሥራ ተጠያቂው አንተና ሰይጣን ሳትሆኑ፣ ይህ እንዲሆን አዳምን ከመፍጠሩ በፊት የወሰነብህ አላህ ነው፤ ማለት ነው፡፡ እራሱ የአንድን ሰው ፍጻሜ ምን መሆን እንዳለበት ከወሰነ በኋላ፣ ተመልሶ ከእነርሱ መልካም ነገር እንዴት ይጠብቃል? ይህ ምን አይነት አምላክ ነው? የትኛውስ አዕምሮ ነው መሀሪ አምላክ ማለት እንዲህ አይነት ይሆናል ብሎ የሚያምን? እስኪ አሁን ደግሞ ነቢዩ ወደተናገሯቸው ሐዲሶች ልለፍ፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 23 ፡ 334 ቅጽ 2**

ነብዩን ከሚረዱትና ከሚደግፉት ከአንሳር ጎሳ የሆነችው **የአል–አላ** እናት ስትነግረኝ፣ ስደቶኞች ለህዝቡ በእጣ በተከፋፈሉ ጊዜ **ኡስማን ቢን ማዙን** ደረሰን፡፡ ከእኛም ጋር እነዲኖር ወደቤታችን ወሰድነው፡፡ ከዛ በፀና ታሞ ሞተ፡፡ እንደሞተም አጠብነውና በራሱ ልብስ ከፈነው፡፡ የአላህ መለልእክተኛ ሲመጡ እኔ፦ "**አ አቡ ሳይብ አላህ** ምህረት የተሞላ ይሁንልህ! **እርሱ በክብር እንደሚቀበልህ እርግጠኛ ነኝ፤" ስል ተናገርኩ፡፡** ነብዩም አላህ በክብር እንበሚቀበለው እንዴት አወቅሽ? አሉኝ፡፡ እኔም አባቴ ስለ እርስዎ ቤዛ ይሁን! የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አላህ በክብር የሚቀበለው ማንን ነው ታዲያ? አልኳቸው፡፡ ነብዩም ምንም ችግር የለውም፤ ሞት ወደ እርሱ መጥቷል፤ እኔም መልካሙን እመኝለታለሁ፡፡ ነገር ግን **እኔ የእርሱ መልእክተኛ ሆኘ ከሞት በኋላ በእኔ ላይ ምን እንደሚያደርግ እንኳን አላውቅም፡፡ በአላህ! ከሞት በኋላ ስለ ማንም መዳን በፍጹም ማረጋገጫ የለኝም**

**ጃብር ኢብን አብደላህ** የተናገረው

**ሳሂህ ሙስሊም 4 ፡ 2073**

ሰዎች አስከሬን ተሸክመው ሲያልፉ ለሟቹ በመልካም ቃላት እያደነቁ ይናገሩ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ ሶስቴ በእርግጥ ይሆናል እያሉ ተናገሩ እንደገናም ሰዎች አስከሬን ተሸክመው አለፉ እነዚህም ስለ ሟቹ በክፉ ቃል እየተናገሩ ይወቅሱት ነበር፡፡ በዚህ ላይም የአላህ መልእክተኛ ይህ በርግጥ ይሆናል ሲሉ ሶስቴ ደጋግመው ተናገሩ፡፡ ኡመርም የአላህን መእክተኛን አባቴ እና እናቴ ስለ እርስዎ ቤዛ ይሁኑ! አስክሬኑን ሰዎች ተሸክመው ሲያልፉና በመልካም ቃላት እያሞገሱ ሲናገሩለት እርስዎ ሶስቴ በእርግጥ ይሆናል አሉ፡፡ ደግሞም እንደገና ሰዎች አስክሬን ተሸክመው እያለፉ ለሟቹም በክፉ ቃላት እየተናገሩና እየወቀሱት ሲያልፉ እርሶም ሶስቴ በእርግጥ ይሆናል

አሉ አላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ እናንተ በመልካም ቃላት እያወደሳችሁ የምትናገሩለት ሟች ገነት መግባት ለእርሱ በእርግጥ ይሆንለታል፣ በክፉ ቃላት እየተናገራችሁ የምትወቅሱት ሟች ደግሞ ገሀነም መግባት **ለእርሱ እርግጥ ይሆንበታል፡፡** **እናንተ በምድር የአላህ ምስክሮች ናችሁ ሲሉ ሶስቴ ደጋግመው ተናገሩ፡፡**

## አናስ ቢን ማሊክ የተናገረው

ወንድሜ አህመድ የነብዩ ሃዲስ አንዱ ከሌላው የሚቃረን ቢሆንም ጀነት የመግባት ጉዳይ በሰው ምስክርነት የሚረጋገጥ ከሆነ ነብዩ የአል አላን እናት እንዴት ሊቃወሚት ቻሉ? በእርሳቸው ላይስ ምን እንደሚያደርግ ያለወቁት ለመልካምነታቸው መስካሪ የሚሆን ሰው ስለሌለ ነውን? ድፍን ሙስሊሙ ማህበረሰብ የትሄዶ ነው? ወይስ ሙስሊሞቹ የሚሰጡት ምስክርነት በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ስለሌለው ይሆን? ግራ አጋቢ ነገር አልሆነብህም???? **ደግሞም** አላህ **በሱረቱል** መርየም ላይ ሁሉም ሙስሊሞች ጀነት እንደማይገቡ የተናገረውን እስኪ ላስነብብህ፦

**ሱረቱል መርየም** 19 ፡ 71
ከእናንተም ወደ እርሷ ወራጅ እንጂ አንድም የለም፡፡ (መውረዱም) ጌታህ የፈረደው ግዴታ ነው፡፡

وَإِن مِّنكُمْ إِلَّا وَارِدُهَا ۚ كَانَ عَلَىٰ رَبِّكَ حَتْمًا مَّقْضِيًّا

አላህ በመፍጠር ጅማሬ ላይ ከአዳም ልጆች ጋር ስለላከናወነው አንድ ውል **ሱረቱል አል–አዕራፍ** 7 ፡ 172-173 ይተርካል፡፡ ይህን በፍጥረት ጅማሬ ላይ የተካሄደውን የአላህንና የአዳም ልጆችን **የአምላክ ማነው?** የኪዳን የውል ስምምነት ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር፣ **ኢማም ኢብን ካሲርና ሳሂህ የሆኑት ሐዲሳትም** ስለ አንቀጹ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት በድራማዊ መልክ አስፍረውታል፡፡ ሐዲሱም እንዲህ ይነበባል፦

**ተፍሲር ኢብን ካሲር ሱረቱል አል-አዕራፍ** 7 ፡ 172-173
**ሳሂህ አል–ቡኻሪ** 55 ፡ 551 **ቅጽ** 4
**ሱና መሊካ ሙዋታ** 46 ፡ 2

.....**ስለ ሱረቱል አል-አዕራፍ** 7 ፡ 172 ተጠይቀው ሲመልሱ ሰምቻለሁ፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሲመልሱ፦ የተባረከውና ከሁሉም በላይ ከፍ ያለው አላህ አዳምን ፈጠረ፣ ከዛም በቀኝ እጁ ጀርባውን መታ ሲያደርገው የወደፊት ዘሮቹ ከእርሱ ወጡ፡፡ አላህም እነዚህን **ለገነት ፈጥሬአቸዋለሁ፣ እንደ ገነት ሰዎችም ተግባራቸው ይሆናል አለ፡፡** እንደገናም ጀርባውን መታ ሲያደርገው ቀሪ ሌሎች የወደፊት ትውልዶቹ ከእርሱ ወጡ፡፡

አላህም እነዚህን ደግሞ ለእሳት ፈፍሬአቸዋለሁ፤ እንደ ገሃነም ሰዎች ተግባራቸው ይሆናል አለ፡፡ ጠያቂውም የአላህ መልእክተኛ! እንዲህ ከሆነ የሥራዎቻችን ዋጋ ምንድን ነው? አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሲመልሱ፡- አላህ ባሮቹን ለገነት ሲፈጥር የገነት ሰዎችን ባህሪ እንያደርጉ አድረጎ ነው፤ ስለዚህ ሲሞት ከአንድ የገነት ሰዎች ሥራ ጋር ይሞታል፤ በዚህም አላህ ወደ ገነት ያመጠዋል፡፡ ለገሃነም የፈጠረውን ባሪያውን ደግሞ የገሃነምን ሰዎችን ሥራ እንዲያደርግ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ሲሞት ከአንድ የገሃነም ሰዎች ሥራ ጋር ይሞታል፤ በዚህም ወደ ገሃነም ያመጣዋል፤ አሉ፡፡

ኡመር አል–ኸታብ የተናገረው ሃዲስ

**ሲራ ኢብን ሳድ ኪታብ አል-ጠበቃት ቅጽ 1፣ ክፍል 1.3.23**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቻልሁ፡- አላህ አዳምን ፈጠረው፤ ከዛም የወደፊት ዘሮቹን አወጣና እንዲህ አለ፡- እነዚህን የጀነት ይሆናሉ፤ እኔ ግድ የለኝም፡፡ እነዚህኞቹ ደግሞ ለጀሃነም ይሆናሉ፤ እኔ ግድ የለኝም አለ፡፡ አንድ ሰው ታዲያ ለምን መልካም ሥራ እንሠራለን? ብሎ ጠየቀ፡፡ ነቢዩም ወደተወሰነላችሁ ለመድረስ አሉ፡፡

ይህ ቀዷ ወቀድር የሚባለውን አስተምህሮ ያሳያል፡፡ ከእስልምና የእምነት መሰረቶች መካከል አንዱ በቀዷና ቀድር ማመን ነው፡፡ የእነዚህም ሁለት ቃላት ትርጉምና አስተምህሮ የእስልምና መሰረት ሀሳቦች ክፍል ሁለት በተባለው መጽሃፍ ከገጽ 90–104 ላይ እንደሚከተለው ሰፍሯል ፦

ቀዳእ ማለት፦ «አላህ ጥንቱኑ በአጠቃላይና በዝርዝር ነገሮችን ሁሉ በእውቀቱ ስር ማጠቃለሉንና የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ ከእርሱ መሻት የሚመነጩ ናቸው፡፡»

ቀድር ማለት «በተፈጥሮ ውስጥ የሚደረጉና የተደረጉ ነገሮች ሁሉ አላህ ጥንቱኑ በሻው መሰርት የተወሰኑ ህግጋትንና ደንቦችን በመከተል ምንም ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ የሚደረጉ (የሚፈጠሩ) መሆናቸውንና ከእርሱ መሻት ውጭ በዱብ እዳ የሚሆን ነገር አለመኖሩን ያሳያል፡፡»

ነገሩን ግልጽ እንዲሆንልን በዛው የተሰጡ ተጨማሪ አሳቦችንና ማብራሪያዎችን ልጨምር፦

«የሰው ልጆች መሻት በአላህ መሻት ውስጥ ነው፡፡..... ምዕመናን በፍላጎታቸውና በምርጫቸው አላህ እንዲሰሩት የሚሻውን ብቻ ይሰራሉ፡፡ ሱረቱል አል-ተክዊር 81 ፡ 27–29 »

**«ቀዷ እና ቀድር ከአላህ እውቀት፣ ከርሱ መሻትና ከኃይሉ ጋር የተያያዘ ሲሆን የሚገለጸውም በሰዎች ሥራ ውስጥ ነው፡፡** ሰልማን የተባሉ የነብዩ ባልደረባ (ሱሃቢይ) ስለዚህ የእምነት መሰረት ተጠይቀው ሲመልሱ፡- የደረሰብህ የማይቀርልህ፤ ያልደረሰብህ የማያገኝህ እንደ ነበር ማወቅ ማለት ነው፤ ብለዋል፡፡ በቀድር ማመን ማለት አላህ ያለልህ የመይቀር፤ ያላለልህ የማይደርስብህ መሆኑን ማመን ማለት ነው፡፡ በቀድር የማመን ግዴታ በሁለት ይከፈላል፡-

1. **አላህ ጥንቱኑ ሰዎችን መፍጠሩና ከማስገኘቱ በፊት** <u>**መልካም ሆነ መጥፎ መመራትትም ሆነ መጥመም መታዘዝም ሆነ ማመጽ**</u> በአጠቃላይ የሰዎችን ሥራ በሙሉ ከነሱ ማን የገነት መሆኑን፣ ማንስ የገሃነም እንደሆነ ሙሉ በሙሉ በእውቀቱ ስር የአጠቃለለ መሆኑን፣ ከመፈጠራቸው በፊት ለሥራዎቻቸው ምንዳን እና መቀጣጫ ያዘጋጀላቸው መሆኑን፣ ይህን ሁሉ <u>**ጥንቱኑ አዘጋጅቶና ወስኖ የጻፈ (የፈረደ) መሆኑን ማመን፡፡**</u>
2. አላህ የሰዎችን ሥራዎችን፣ እምነታቸውን፣ ክደታቸውን፣ ታዛዥነታቸውንም ሆነ አመጸኝነታቸውን ሁሉ የ<u>**ፈጠረና በእነርሱም ላይ የሻ መሆኑን፤ ግን ከሰዎች ኃጥአትን የማይቀበል፣ ኃጥአት እንዲሰሩ የማያዝ መሆኑን ማመን ነው፡፡»**</u>

ይህ የቀዷ ወቀድር የእምነት አንቀጽ ትርጉም እንዴት እርስ በእርሱ እንደሚቃረን እያስተዋልክ ያለህ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተጨማሪ ሐዲሳትም እስኪ ላስነብብህ፡-

**ሳሂህ አል–ቡኻሪ** 55 ፡ 549 **ቅጽ** 4
**ሳሂህ አል–ቡኻሪ** 23 ፡ 444
**ሳሂህ አል–ቡኻሪ** 77 ፡ 602

ከነብዩ ጋር አብረን ተቀምጠን ሳለን እንጨት በእጃቸው ይዘው መሬት ላይ ይጽፉ (ይጭሩ) ነበር፡፡ እንገታቸውን አዘንብለው እንዲህ አሉ፡- **«ከእናንተ መካከል ከተወሰነለት ውጭ የሚሆን ማንም የለም፤ ወይ የገሃነም ወይ የገነት ናችሁ፡፡** ያኔ ከሰዎቹ መካከል አንዱ እንዲህ አለ፡- የአላህ መልእክተኛ <u>ከዚህ ውጭ ምንም ተስፋ የለንም?</u> የለም፣ ነገር ግን <u>ሥራችሁን መስራታችሁን ቀጥሉ፤ ለእያንዳንዱ ሰው ወደ ተወሰነለት ስፍራው የሚመራው ሆኖ ስራው ቀሎለት ያገኘዋል አሉ፡፡</u>
አሊ የተናገረው

**ሳሂህ አል–ቡኻሪ 76 ፡ 470 ቅጽ 8**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰማሁ፦ <u>**«ማንኛውም ሰው በመልካም ሥራው ወደ ጀነት አይገባም፡፡»**</u> የነብዩ ሱሃባዎችም <u>**"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርስዎም ቢሆኑ በመልካም ሥራዎት አይገቡምን?"**</u> አሏቸው፡፡ ነብዩም <u>**«አዎን አላህ ምህረቱን ካላበዛልኝ በስተቀር ሥራዬ እኔንም አያስገባኝም፡፡**</u> ስለዚህ መልካምን ሥራ በትክክል ሥሩ፤ አላህን በጠዋት፣ በቀን፣ በምሽትም፣ በመካከልም ሁልጊዜ በትክክል አምልኩት፤ ከዛ ከግባችሁ ትደርሳላችሁ፡፡

አቡ ሁሬይራ የተናገሩት

**ሱና ማሊክ ሙዋታ 46 ፡ 1**
**ሳሂህ አል–ቡኻሪ 60 ፡ 262 ቅጽ 6**
**ሳሂህ አል–ቡሃሪ 77 ፡ 611 ቅጽ 8**

ነብዩ እንዲህ አሉ፦ **አዳምና ሙሴ** እርስ በእርሳቸው ተወቃቀሱ፣ **ሙሴ አዳምን አዳም ሆይ!** እንድንሰቃይና ከገነት እንድንባረር ያደረግህ አባታችን አንተ ነህ፤ አለው፡፡ አዳምም አላህ ፊት ለፊት ያናገረህና ተውራቱን በራሱ እጅ ጽፎ የሰጠህ ሙሴ ሆይ! <u>**አላህ እኔን ከመፍጠሩ ከአርባ አመት በፊት ወስኖ የጻፈብኝን ኃጢአት በፈጸምኩ፤ እኔን ተጠያቂ ታደርገኛለህን?**</u> ሙሴ ተሳስተሃል ሙሴ ተሳስተሃል አለው፡፡ ይህንንም ንግግር ነብዩ ሶስቴ ደገሙት፡፡

**አቡ ሁሬይራ የተናገሩት ሃዲስ**

እስኪ አንድ ሃዲስ ልጨምርና ወደ ሌላው ልለፍ፦

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 93 ፡ 546 ቅጽ 9**
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 55 ፡ 549-554 ቅጽ 4**
**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 77 ፡ 593 ቅጽ 8**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- ከእናንተ እያንዳንዱ በእናቱ ማሕጸን ለአርባ ቀናት ይሰባሰባል፣ ከዛም በኋላ ወደረጋ ደምነት ይቀየራል፤ ከተመሳሳይ አርባ ቀን ቆይታ በኋላ ቁራጭ ሥጋነት ይቀየራል፡፡ ከዛ በኋላ አላህ መልአክ ይልካል አራት ነገሮችን እንዲጽፍ ያዘዋል፡፡ የወደፊት ኑሮውን፣ እድሜውን <u>**በኋለኛው ዘመን የተባረከ ወይንም እርጉም መሆኑን ይጽፉል፤**</u> ከዛ በኋላ ነፍሱን ይነፋበታል፡፡ በአላህ ከእናንተ መካከል አንዱ የገሃነምን ሰዎች ሥራ በእርሱና በገሃነም መካከል አንድ ክንድ ድረስ ቢሰራ፣ ከዛ አላህ መልአኩን አዞ ቀድሞ የጻፈውን የገነት ሰዎችን ሥራ ይሠራና ገነት ይገባል፡፡ ደግሞ አንዱ የገነት ሰዎችን ሥራ

በገነትና በእርሱ መካከል አንድ ክንድ እርቀት ድረስ ቢሰራ ከዛ በኋላ አላህ መልአኩን አዞ ቀድሞ የተጻፈበትን የገሃነም ሰዎችን ሥራ ይሠራና ገሃነም ይገባል፡፡

አብዱላ ኢብን መሱድ የዘገበው

ወንድሜ፡- እዚህ ላይ አንዴ ላቁምና ከእስካሁኑ ንባብ ምን እንዳስተዋልክ ልትነግረኝ ትችላለህ? ግንዛቤህን ለማስፋት አንዳንድ ጥያቄዎችን እስኪ ልጠይቅህ፡-

- የአላህን ባህሪ ገላጭ እንደሆኑ የሚነገርላቸውን 99 ስሞቹ የሚያስተላልፉትን ባህሪያት በእነዚህ የሐዲሳቱና የቁርአኑ አንቀጾች ውስጥ ማየት ችለሃል? አል-ረሂም፣ አል-አድል፣ አል-ሐኪም የሚባሉትን ማለቴ ነው፤
- ቁርአን የአላህ ቃል ከሆነ፣ እነዚህ ከነቢዩ አንደበት የወጡ ሐዲሳትና የቁርአኑ አንቀጾች ጀነት የመግባትህን ተስፋ ፍንትው አድርገው አሳይተውሃል? በእውነት ከአላህ ምትጠብቀው ትክክለኛ ፍትህ፣ ምህረትና የርህራሄ አምላክነት ይህንን የሚመስል ነበር?
- ሙሴ በአዳም ስህተት የሰው ልጆች ሁሉ ከጀነት በመባረር፣ በምድር ላይ በመከራ ለመኖር እንደተዳረጉ ያምናል፤ አዳምንም አግኝቶ እንደወቀሰው ነቢዩ ነግረውናል፤ አዳምም ለሠራው ስህተት ተጠያቂው አላህ እንጂ እርሱ ወይንም ያታለለው ሰይጣን እንዳልሆነ አረጋግጧል፤ የፈጸመውን የፈጸመው ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው 500,000 ዓመታት በፊት ወይም እራሱ ከመፈጠሩ ከአርባ ዓመታት በፊት በአላህ ሰለተወሰነበት መሆኑን ተናግሯል፡፡ በሐዲሱ ላይ እንዳነበብከው፣ ቁርአንም እንደ ተናገረው ሰዎች ለጀነት ወይንም ለጀሃነም እንዲሆኑ በእራሱ በአላህ ተወስኖባቸው ነው የተፈጠሩት፡፡ ታዲያ አንተ ከየትኛው ወገን እንድትሆን ሆነህ ነው ወደዚህ ምድር የመጣኸው? ውድ አንባቢ እርሰዎስ ከየትኛው ወገን ይሆኑ? አላህ በሰው ልጆች ላይ ይህንን አድርጓል ብለው ያምናሉ? ለምን?
- አላህ የፍትህ አምላክ ነው፤ ተብሎ ስሙ አል-አድል ተብሏል፤ እስካሁን ባነበብካቸው ሐዲሳትና የቁርአን አንቀጾች ማየት የቻልከው ፍትዊነቱን ወይንስ ፍትህ አልባነቱን? እራሱ ለጀሃነም እንዲሆኑ አስቦ ፈጥሯቸው እያለ፣ ይህንንም እያወቀ፣ እንደገና የተወሰነባቸውን በፈጸሙ እንደ ወንጀለኛ በገሃነም መቅጣቱ እውነተኛ ዳኛ ያሰኘዋል?
- ሐዲሱ ላይ እንደሚታየው አንድ ሰው ለጀነት ተፈጥሮ እያለ የገሃነም ሰዎችን ሥራ መሥራት ከቻለ አላህ የተዋጣለት፣ ያለውም የሚሆንለት ፍጹም አምላክ ነው፤ ማለት ይቻላል? ነው ወይስ አላህ ፍጹም የማይሳሳትና ያለው የሚሆንለት አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ቁርአንና ሐዲሳቱ ማንነቱን ያጎደፉት ይሆን? ታዲያ እንዲህ ከሆነ ነቢዩ ሙሐመድና ቁርአን የአላህን ፍትሐዊ አምላክነት ማሳዬት የቻሉና ከአላህ በእዝነቱ የተላኩ ናቸው ብለህ ታምናለህ?

ወንደሜ ሆይ! አላህ እንዲህ አይነት የአምላክንና የሰው ልጆችን የፍትህ ትርጉም ሊያሟላ የማይችል የፍትህ መጓደል በሰው ልጆች ላይ ይፈጽማል ተብሎ አይታመንም፡፡ ይህ የቀዷ ወቀድር አስተሳሰብ፣ የአላህን የፍትህ አምላክነት ይጻረራል በመባሉ እስልምናን ከሁለት መክፈሉን ሳትሰማ የምትቀር አይመስለኝም፡፡ የአላህን ፍትሀዊ አምላክነት የሚጻረር እንዲህ አይነት የኢማን አንቀጽ አንቀበልም በማለታቸው በርካታ ሙስሊሞች በሌሎች ሙስሊም ወንድሞቻቸው ተገድለዋል፡፡

- አላህ ሰዎች መልካም ሥራንና ኃጢአት እንዲሠሩ ቀድሞ የጻፈባቸው ከሆነ፤ እንዲሁም መልካምም ሆነ ክፉ እንዲሆንባቸው የጻፈባቸው እራሱ ከሆነ፤ በምድር ላይ ያለው የመልካምና የክፉ፣ የኃጢአትና የጽድቅ ሥራ ሁሉ ምንጪ እራሱ ነው ማለት ነው፡፡ ታዲያ የሰውን ልጆች ለማሳት ዝቶ፣ አላህም ፈቅዶለት ከገነት የወጣው የሰይጣን የሥራ ድርሻ ምንድን ነው? ሰይጣን በሰዎች ላይ በሚሆኑት ነገሮች እንደ ክፉ አድራጊ የሚቆጠረው ለምንድን ነው? ሁሉም ነገር በአላህ ውሳኔ /ቀድር/ መሰረት እንደሚከናወን የሚታመን ከሆነ፣ አዳም እንደተናገረው ኃጢአት የሚደረገው በአላህ ስለተወሰነ እንጂ፣ ሰይጣን የነገሮቹ ምንጭ ስለሆነ አይደለም፤ ወደሚል መደምደሚያ ይወስደናል፡፡ ታዲያ የሰው ልጆች ጠላት መባል ያለበት ሰይጣን ወይንስ አላህ? ሰይጣን የሰው ልጆችን የጽድቅ መንገድ ለማጥመም ዝቶ ከአላህ ፊት ተፈቅዶለት እንደወጣ ከሚናገሩት የቁርአኑ አንቀጾች ጋር እየተሳከረ ያለ አይመስልህም?
- እንደ ቀድዋ ቀድር አተረጓጎም አንተ የምታመልከው አላህ የሁለቱም ማለትም የኃጢአትና የጽድቅ መፍለቂያ ምንጭ ከሆነ፤ እንዲህ ያለ አምላክ እንከን የማይወጣለት ንጹህ አምላክ ነው ማለት ትችላለህ? እንዲህ ነው የምታምነው? መጽሐፍ ቅዱስ ግን አላህ ከዚህ ውጭ የሆነ አምላክ እንደሆነ ያስተምራል፤ እኔም የማምነው ያንን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አላህ ከሚናገረው እስኪ ትንሽ ላስነብብህ፡-

**1ኛ የዮሐንስ መልእክት 4 ፡ 9-10**

በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።

**1ኛው የዮሐንስ መልእክት 4 ፡ 16**

እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።

**1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች** 13 ፡ 4-7

ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።

**ትንቢተ ናሆም** 1 ፡ 7

እግዚአብሔር መልካም ነው፥ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው በእርሱ የሚታመኑትንም ያውቃል።

**የያዕቆብ መልእክት** 1 ፡ 16-18

የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ አትሳቱ። በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ። ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።

- ወንድሜ! እንዴ ወደኋላ ልመልስህና ከነቢዩ ሙሐመድና ከአንሳሪዋ የአል-ኣላ እናት ትክክለኛው የእምነት ትርጉም የሚንጸባረቀው በማን ይመስልሃል? ለእኔ ብትጠይቀኝ መልሴ የአል-አላ እናት ላይ የሚል ነው፤ ነቢዩ ላይ ምንም አላየሁባቸውም፡፡ ይሁንና ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ ነቢይ ሆነው ከሞት በኋላ አላህ ምን እንደሚያደርግባቸው ማዎቅ ካልቻሉ፣ የማመን መለኪያ ምንድን ነው? ያመኑትስ ምንድን ነው? የማመናቸው ጥቅም ምንድን ነው ትላለህ? በአላህ መኖር ማመን? እርሱንማ የድንቁርና ዘመን ተብሎ በሙስሊሞች በሚጠራው ዘመን የኖሩ አረቦችም ያምኑ እንደነበር ቁርአን እራሱ ይናገራል፤ መጽሐፍ ቅዱስም ሰይጣንም ያምናል ይላል /**የያዕቆብ መልእክት** 2 ፡ 19/፡፡ ሰው አመንኩ የሚለው እርግጠኛ በሚሆንበት ነገር ላይ ነው፡፡ ታዲያ እርሳቸውን እርግጠኛ ያላደረገ የሃይማኖት መንገድ እንዴት አንተን እርግጠኛ ሊያደርግህና መንገዱን ከሌላው ይልቅ ተመራጭ ሊያደርግልህ ይችላል? አያድርስና አሁን ብትሞት ያለምንም ጥርጥር ጀነት እንደምትገባ እርግጠኛ ነህ? ውድ

አንባቢ እርሰዎስ እርግጠኛ ነዎት? **በሱረቱል መርየም** 19 ፡ 71 ላይ ወደ ገሃነም መውረዳችሁን በማያዳግም ቃል እርግጥ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ጀነት መግባታችሁን እርግጠኛ የማያደርግ እምነት ውስጥ ካላችሁ፤ ከእውነተኛው አምላክ ጋር ላለመሆናችሁ እርግጠኞች መሆን የለባችሁም? እምነት እርግጠኛ ያደርጋል፤ እምነት ማለት ምን ማለት መሰለህ፡-

**ወደ ዕብራውያን ሰዎች** 11 ፡ 1

እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት በመከተል ገነት መግባትን እንዴት እርግጠኛ እንደሚያደርግ፣ እርሱንም በእምነት መከተል ዝም ብሎ በጭፍን የሚጓዙበት መንገድ አለመሆኑን የገለጸበትን ክፍል ላስነብብህ እፈልጋለሁ፡-

**የዮሐንስ ወንጌል** 3 ፡ 16-18

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።

**ወደ ሮሜ ሰዎች** 8 ፡ 1-2

እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።

አንዴ ነቢዩ ሙሐመድ ለተከታዮቻቸው የሚከተለውን አሏቸው፡-

**ሳሂህ ሙስሊም** 39 ፡ 6757
**ተፍሲር ኢብን ካሲር ሱራ** 113-114

ከእናንተ ሰይጣን ያልተመደበበት አንድም የለም አሏቸው፤ እነርሱም የአላህ መልእክተኛ እርስዎስ? ሲመልሱም አዎን አለኝ፤ ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና አሸነፍኩት፡፡ እርሱም ሰልሟል፣ አሁን የሚያዘኝ መልካም እንድሠራ ነው፡፡

**ሐዲስ ሚሽካት አል-ሙሳቢህ ም 27፣ ክፍል 19፣ ቁ 131፣ ቅጽ 2**

*ባሏ ሳይኖር ሴትን አትጎብኙ፤ ምክንያም ሰይጣን ደም እንደሚዘዋወር እንዲሁ በውስጣችሁ ይሯሯጣልና አሉ፡፡ እኛም የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በእርስዎም ውስጥ ይሯሯጣልን? ስንል ጠየቅናቸው፡፡ እርሳቸውም አዎን፤ በእኔም ውስጥ ይሯሯጣል፡፡ ነገር ግን አላህ በእርሱ ላይ እረዳኝና ተገዛልኝ አሉ፡፡*

*ጃብር የተናገረው ሐዲስ ነው፡*

- *ወንድሜ አህመድ! ሰይጣን የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት እንደሆነ ቁርአን ይናገራል፤ ታዲያ የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት የሆነው ሰይጣን በውስጡ እንዳለበት፣ እርሱን የሚከተሉትም በአጠቃላይ ሰይጣን በልባቸው እንዳለባቸው የሚያምን ነቢይ የአላህ መልእክተኛ ነው ብለህ ታምናለህ? ገብቶሃል? አንተም አለብህ እያሉህ ነው፤ እርግጥ ነው? ውድ አንባቢ ሙስሊም ከሆኑ ነገሩ እርስዎንም ይጨምራል፤ እንደ ነቢዩ ሙሐመድ እርስዎም ሰይጣን እንዳለበዎት ያምናሉ?*

እስኪ ሌላም ሐዲስ ላስነብባችሁ፡-

*ኡመር ኢብን ኸታብ በእምነቱ ጠንካራ፣ በአቂዳ ጽኑ የሆነና ዲኑን በደንብ የሚጠብቅ ሰው ነበር፡፡ እርሱ አላህ የመደበበትን ሰይጣን ተጽእኖ በማድረግ ማስለም አልቻለም፡፡ ነገር ግን አላማው እንዲፈራው ማድረግ ነበር፡፡*

*የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ አማኞች ከአላህ የተመደበባቸውን ሰይጣን ማስለም በጉዟቸው ላይ ያለን ትልቅ ተራራ እንደመውጣት ይቆጠራል፡፡*

*አቡ ሁሬይራ የተናገረው ሐዲስ*

- *ወንድሜ እስኪ ደግሜ ልጠይቅህ፡- ነቢዩ እንዳሉት በአንተ ልብ ውስጥ አብሮ የሚኖር፣ የሚመክር፣ ስራህን የሚያጣድፍ ሰይጣን እንዳለብህ قَرِينُه ታምናለህ? ታዲያ ሰይጣን ካለብህ ከአላህ ጠላት ጋር እየኖርክ በእውነት ጎዳና ላይ ነኝ ለማለት እንዴት ትችላለህ?*
- *እሺ፤ አንተ ሰይጣንህን ምን እንዲሆንልህ ነው ተጽእኖ የምታደርግበት? እንደ ነቢዩ ሰይጣን እንዲሰልም ወይንስ እንደ ከሊፋ ኡመር ሰይጣን እንዲፈራህ? በልብህ እየኖረስ እንዴት ነው የሚፈራህ?*
- *እስልምና ከተጀመረ አንድ ክፍለ ዘመን አልፏል፤ ከመካከላቸው የሰለሙ እንዳሉ ቁርአን በሱረቱል አል-ጂን ላይ ግልጽ አድርጎልናል፡፡ ታዲያ ለአንተ የደረሰህ የሰለመ ሰይጣን ወይንስ*

ያልሰለመ? ውድ አንባቢ የእርስዎስ ምን አይነት ነው? ምን እንዲሆንለዎት ነው የሚፈልጉት?

- እውነት ይህ መንገድህ ከአላህ የተሰጠ እውነተኛ መንገድ ነው፤ ብለህ ታምናለህ? አዎን ከሆነ መልስህ ምን አይነት ከራሱ ቃል ጋር የሚጣረስ አላህ ነው የምታመልከው?
- በድጋሚ፤ ሰይጣን እንደአለበት የሚያምን፣ በእርሱም የሚታዘዝ መልእክተኛ የአላህ መልእክተኛ ይሆናል ብለህ ታምናለህ? ሰይጣን ማን ነው? መልካም ነገር ከእርሱ ይገኛል? ይህስ ከቁርአን ጋር መጋጨት አይሆንም? ምን አይነት የተመሰቃቀለ ነገር ነው? እስኪ ከሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ጋር አስታርቅልኝ፡፡ በነገራችን ላይ ይህንን ስል ስለ ጂን እስልምና የሚያስተምረውን ዘንግቸ ወይንም ስለማላውቅ አይምሰልህ፡፡ ጊዜ ስናገኝ ስለሱ በሰፊው እናወራለን፤ አሁን የቁርአኑን አንቀጽ ላስነብብህ፡-

**ሱረቱል ፋጢር 35 ፡ 6**

ሰይጣን ለናንተ ጠላት ነው፡፡ ስለዚህ ጠላት አድርጋችሁ ያዙት፡፡ ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ጓዶች እንዲኾኑ ብቻ ነው፡፡

إِنَّ الشَّيْطَانَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَاتَّخِذُوهُ عَدُوًّا ۚ إِنَّمَا يَدْعُو حِزْبَهُ لِيَكُونُوا مِنْ أَصْحَابِ السَّعِيرِ

- ነቢዩ ሙሐመድ የተመደበብህን አንድ ሰይጣን ማስለም ተራራን ከመውጣት ጋር በማመሳሰል እንደማይቻል አሳይተዋል፤ ታዲያ አንተ የተመደበብህን ሰይጣን አሸንፈህ ማስለም የምትችል ይመስልሃል? ካልሰለመ ደግሞ ወደ ጥፋት መምራቱ ስለማይቀር ጀነት የመግባት እድልህ ዜሮ ከመቶ መሆኑ ነው፡፡ ነቢዩ እንኳን አላህ የመደበባቸው ሰይጣናቸው ሰልሞላቸው ጀነት ለመግባታቸው እርግጠኛ አይደሉም፤ ታዲያ አንተ ምን ይሻልሃል ሌላ ተስፋ ይኖርሃል? እንዴት የሚያስጨንቅ ጨለማ ነው እባክህ?
- የቁርአን ባለቤትና ተናጋሪው አላህ ከሆነ ሰይጣን ለአዳም አልሰግድም ብሎ በተዛባ ፍርድ ከገነት እንዲባረር በተደረገበት ወቅት ከአላህ ጋር የሚከተለውን ተነጋግረው ነበር፡-

**ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 39-40**

(ኢብሊስ) አለ ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ ይኹንብኝ ለነርሱ በምድር ላይ (ኀጢአትን) እሸልምላቸዋለሁ፡፡ ሁሉንም አጠማቸዋለሁም፡፡ «ከነርሱ ፍጹሞቹ ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡»

قَالَ رَبِّ بِمَا أَغْوَيْتَنِي لَأُزَيِّنَنَّ لَهُمْ فِي الْأَرْضِ وَلَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ الْمُخْلَصِينَ

**ሱረቱል ሷድ 38 ፡ 82-85**

**(እርሱም) አለ በአሸናፊነትህ ይኹንብኝ፤ በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡ «ከእነርሱ ምርጥ የኾኑት ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡» (አላህ) አለው «እውነቱም (ከኔ ነው)፡፡ እውነትንም እላለሁ፡፡ ከአንተና ከእነርሱ ውስጥ ከተከተሉህ ባንድ ላይ ገሀነምን በእርግጥ እሞላታለሁ፡፡»**

قَالَ فَبِعِزَّتِكَ لَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ الْمُخْلَصِينَ قَالَ فَالْحَقُّ وَالْحَقَّ أَقُول لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكَ وَمِمَّن تَبِعَكَ مِنْهُمْ أَجْمَعِينَ

**ሱረቱል አል-ኢስራ 17 ፡ 65**

**«ባሮቼ በእነሱ ላይ ፊጽሞ ላንተ ስልጣን የለህም፡፡ መጠጊያም በጌታህ በቃ፡፡»**

إِنَّ عِبَادِي لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَانٌ ۚ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ وَكِيلًا

ውድ ወንድሜ እስኪ አሁንም ልጠይቅ፡-

- በእነዚህ ከላይ ባነበብካቸው የቁርአን አንቀጾች ላይ እንደ ሚታየው ሰይጣን የአላህን ባሮች እንዳይነካ ታዞ ከገነት ወጥቷል፡፡ እርሱም ቢሆን በዚህ ጉዳይ አምኖበት እነርሱን ላይነካ፣ ሌሎቹን ግን ሊያጠማቸው ዝቶ ከአላህ ፊት ወጥቷል፡፡ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ሰይጣን ነቢዩ ሙሐመድንና መላውን ሙስሊም ማሕበረሰብ ከመንካት አልፎ በልባቸው ውስጥ ተንሰራፍቶ በመኖር አመራር በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ እንዲህ እየሆነ ያለው ነቢዩ ሙሐመድና ሙስሊሙ ማሕበረሰብ የማን ባሪያዎች ቢሆኑ ነው? ሰይጣን የተፈቀደለት የራሱ በሆኑት ላይ ብቻ ከሆነ እናንተ ሁላችሁ የሰይጣን ናችሁ ማለት ነው?
- ሰይጣን በ**ሱረቱል አል-ሒጅር** 15 ፡ 40 ላይ ፍጹም የሆኑትን የአላህ ባሮች እንደማይነካ ለአላህ ቃል ገብቷል፡፡ በዚሁ ቃል መሰረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና እናቱን ማርያምን መንካት እንዳልቻለ በሐዲሱ ተገልጾ ይገኛል፡፡ በአንጻሩ ነቢዩ ሙሐመድ ደግሞ በልባቸው ሰይጣን እንዳለባቸው አምነዋል፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ ማርያምና ነቢዩ ሙሐመድ የአላህ ባሮች ከሆኑ በመካከላቸው ይህ ልዩነት ለምን ተፈጠረ? ነቢዩ ምን አይነት ችግር ቢኖርባቸው ነው እንደ ተራ ሙስሊም ልባቸው የሰይጣን ማደሪያ የሆነው?

እንደ ሌሎቹ ነቢያት ፍጹም ካልሆኑስ አላህ ከእርሳቸው ጋር ነበር፤ ብሎ ለመናገር ያስደፍራል ትላለህ? ገነት የሚገቡት ፍጹማን የሆኑ ሰዎች ብቻ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም፤ ታዲያ እርሳቸው አሁን የት ነው ያሉት ብለህ ታስባለህ?

- ነቢዩ ሙሐመድ ሰይጣናቸው በአላህ እርዳታ እንደ ሰለመላቸውና ወደ መልካም ሥራ እንደሚመራቸው ተናግረዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከቁርአን ጋር ይቃረናል፡፡ ሰይጣን ከገነት ተባርሮ ወደ ምድር የመጣው ለመስለም ሳይሆን የሰውን ልጆች ለማጥመም ነው፡፡ አላህም ሲያስጠነቅቀው ባሮቼን ፈጽሞ እንዳትነካቸው እንጂ በልባቸው እየኖርክ አመራር እየሰጠህ እስልምናን ተቀበል አላለውም፡፡ ግልጽ አድርጎ የተናገረው በአንተና በእነርሱ ገሃነምን እሞላለሁ ነበር፤ አንድም ቦታ ላይ እስልምናን ቢቀበል ተመልሶ ገነት ስለመግባቱ አልተገለጸም፡፡ ታዲያ ሰይጣን በምን ምክንያት ዝቶ የወጣበትን ተቀዳሚ ተግባሩን ለመለወጥ በቃ? አላህስ ሰይጣንን ላይምረው ግን እስከ ጊዜው ድረስ ሊያቆየው ቃል ገብቶለት እያለ፣ እንደገና ለእርሱ ያለውን አቋም በመቀየር ነቢዩ ያሉትን ሁሉ የሚል ይመስልሃል? የሚቀይር ከሆነ ደግሞ አቋሙን ሊለውጥ እንደሚችል ምንም አይነት ፍንጭ የማያሳዩትን የቁርአን አንቀጾች ሁሉ ለምን ተናገረ?
- ቆይ ታዲያ ነቢዩ እንዳሉት አንተም ሰይጣን በልብህ ውስጥ ስላለ የማን ባሪያ ነህ እንበል? ውድ አንባቢ እርስዎስ የማን ባሪያ ነዎት? ሰይጣን በልባቸው የሚኖር ሁሉ የሰይጣን ባሪያዎች ናቸው፤ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ወደ ገሃነም ይሄዳሉ እንጂ ወደ ገነት አይገቡም ይህንን ያልኩት እኔ ሳልሆን ቁርአን እራሱ ነው፡፡

**ሱረቱል ሷድ 38 ፡ 85**

ከአንተና ከእነርሱ ውስጥ ከተከተሉህ ባንድ ላይ ገሀነምን በእርግጥ እሞላታለሁ፡፡»

لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكَ وَمِمَّن تَبِعَكَ مِنْهُمْ أَجْمَعِينَ

የተከበሩ ውድ አንባቢ ውዱን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት በመከተል ጎዳና ላይ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ሳሂህ በሆነው ሐዲስ፣ ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቀጥሎ በተገለጸው መልኩ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ የነቢዩን ንግግር የምጠቅሰው ምን እንዳሉ ለመግለጽ ያህል እንጂ በእርሳቸው ላይ እምነት ስላለኝ አይደለም፡፡ ምስክርነታቸው እንዲህ የሚል ነው፡-

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 54 ፡ 506 ቅጽ 4**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡- ከማርያም ልጅ ከኢየሱስ በስተቀር የሰው ልጆች በሚወለዱበት ሰዓት ሰይጣን በሁለት እጣቶቹ የሕጻኑን ገላ በሁለቱም ጎኑ ይነካዋል፡፡ የኢየሱስን ገላ ለመንካት ሞከረ፤ ነገር ግን አልተሳካለትም፡፡ በእርሱ ፋንታ የእንግዴ ልጁን መሸፈኛ ነካ፡፡ አቡ ሁሬይራ የተናገሩት ሐዲስ ነው

**ሳሂህ አል-ቡኻሪ 55 ፡ 641 ቅጽ 4**

የአላህ መልእክተኛ ሲናገሩ የሰማሁት፡- ከአዳም ልጆች መካከል ከማርያምና ከልጇ በስተቀር በሰይጣን ሳይነካ የሚወለድ የለም፤ ስለዚህ ሕጻኑ ሲወለድ አምርሮ የሚያለቅሰው በሰይጣን በመነካቱ ምክንያት ነው፡፡
ሳይድ ቢን አል-ሙሳኢያብ ከቡ ሁሬይራ ሰምቶ የዘገበው

ውድ ወንድሜ እንደ እኔ እምነት የእስልምና ሃይማኖት አላህ የሰው ልጆችን ለማዳን ቀድሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ከገለጠው የደህንነት ጎዳና ይልቅ ትክክለኛ አማራጭ ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡ ጀነት መግባትህን እርግጠኛ የማያደርግ እምነት፣ አጥፊው ሰይጣን በውስጥህ አለብህ አለብኝ የሚል፣ ንግግሩ ተቀበልኩ ካለው ቃል ጋር የሚጣረስ ነቢይ የሚመራው ሃይማኖት ከአላህ ሊሆን ከቶውን አይችልም፡፡ አላህ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በገለጠው እውነተኛ የሕይወት መንገድ ከሰይጣን ጋር ትኖራለህ ሳይሆን የሚለው ሰይጣንን ትረግጣለህ፤ በሰይጣን ትመራለህ ሳይሆን በአምላክህ እየተመራህ ሰይጣንን ታሳድዳለህ፣ ክፉ ሥራውንም ታፈርስበታለህ፤ በኢየሱስ ስምም ሰይጣንን ከሰዎች ውስጥ ታስወጣለህ፤ ታሸንፈዋልህ እንጂ እርሱን መርታት ዳገት ነው አይልም፡፡

**የሉቃስ ወንጌል 10 ፡ 17-20**

ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት። እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።

**የማርቆስ ወንጌል 16 ፡ 17**

ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስለመሆንና አለመሆን ሲናገር ሰው በክርስቶስ የተገለጠውን ሕይወት ሲቀበል የእግዚአብሔር ይሆናል፤ ሳይቀበል ደግሞ የሰይጣን ይሆናል ይላል፡፡ በአንዴ ሁለቱም ጋር መሆን ግን አይቻልም፡፡ እንደ ነቢዩ ሙሐመድ ለእግዚአብሔር ተገዛሁ እያለ እንደገና ከሰይጣን ጋር ኑሮ አለ አይልም፡፡ ሰይጣን በሰው ልብ ውስጥ አብሮ የሚኖር ከሆነ ያ ሰው ገና የሰይጣን እንጂ የአላህ ሊሆን አይችልም፡፡ ከሰይጣን ጋር እየኖሩ ጀነት መግባት የማይታሰብ ነው፡፡

አሁን ወደ መጠቅለሉ እንምጣ፤ ለእኔ አላህ በባህሪው ከላይ በቁርአንና በነቢዩ ሙሐመድ ሐዲሳት ውስጥ እንዳየነው አይነት አምላክ አይደለም፤ እርሱ የፍትሕና የጽድቅ አምላክ ነው፡፡ በአንድ ጎን የክፋት በሌላው የመልካም ነገሮች ምንጭ አይደለም፡፡ የዘለአለም አምላክ ይቅርና እንዲህ ተለዋዋጭ ባህሪ የሚታይበት ሰው በማሕበረሰቡ ውስጥ እንዴት እንደሚስተናገድ መገመት ትችላለህ፤ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ እንደሚባለወው ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልጽ ይቃወማል፤ እርሱ መልካም አምላክ ስለሆነ የመልካም ነገሮች ምንጭ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው ይለናል፡፡ ክፋት ሁሉ የሚመነጨው ከሰይጣን ልብ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ነቢዩ ሙሐመድም ሆኑ ቁርአን የአላህን ትክክለኛ ማንነት ማሳየት አልቻሉም፡፡ ካልቻሉ ደግሞ ከአምላካችን የተላኩ መልእክተኞች አይደሉም ወደሚል መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ ያደርጋል፡፡ እናም እስልምና ለሰው ልጆች የደህንነት አማራጭ መንገድ ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡ ከአላህ ያልሆነ ደግሞ ከላይ ያነበብከው ሱራ 35 ፡ 6 የሚፈጸምበት ቀጥተኛ መንገድ መሆኑን አምናለሁ፡፡

ውድ አህመድ "አላህ እኛን ለማዳን ከፈለገ ኢየሱስ ክርስቶስን መስዋዕት ሳያደርግ ሊያድነን አይችልም ነበር?" ወደሚለው ጥያቄህ ልመለስ፡፡ ውድ ወንሜ መጽሐፍ ቅዱስ የችሎታ ጉዳይ ሳይሆን የባህሪና የፍትሕ ጉዳይ በመሆኑ አይችልም፤ የመዳን መንገዳችን ይህ ብቻ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል፡፡ እንዲህም ይላል፡-

**ወደ ሮሜ ሰዎች 3 ፡ 25-26**

> እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው ፥ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።

የሰው ልጆችን ከዘለአለም ሞት ለማዳን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የወሰደው እርምጃ ጻድቅና ታጋሽ መሆኑን ያሳየበት ነበር፡፡ ስለዚህ ትክክለኛው፣ ፍትሐዊውና በአሳማኝ ምክንያቶች ባህሪውን ቁልጭ አድርጎ

በሚያሳይ መልኩ የተከናወነ የደህንነት መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ወደ ገነት ለመጓዝ ከየትኛውም መንገዶች ይልቅ ብቸኛና ብቸኛው አማራጭ የሌለው መንገድ ነውና ወደዚህ ሕይወት እንድትመጣ፣ ሁላችሁም ትመጡ ዘንድ በጌታ ስም እጋብዛለሁ፡፡

> **የዮሐንስ ወንጌል 14 ፡ 6**
> ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

<u>**መንገድ ነኝ አለ ጌታ፡-**</u>

እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በገነት በደስታና በሐሴት እንዲኖር ፈቅዶለት እያለ አታድርግ የተባለውን በማድረጉ፤ ያን ከመሰለ የክብር ሥፍራ፣ ልዩ ከሆነው መኖሪያው በራሱ ስህተት እንዲወጣ ተገዷል፡፡ ከዛን ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ መንገዱን ይፈልጋል፤ መንገድ ነው ብሎ ባሰበውም ወደዛው በመንጎድ ላይ ነው፡፡ የሰው ልጆች ወደ መጀመሪያው መኖሪያቸው መመለስ ይፈልጋሉ፤ ይህንን የተረዳው ሰይጣን በውስጣቸው ያለውን የመመለስ ፍላጎት ማጠፋፋትና አስሮ ማስቀመጥ ባይቻለውም፣ አንድ ነገር ማድረግ ግን ተችሎት እናያለን፡፡ ብዙ የሆኑ ሃይማኖት የሚባሉ መንገዶችን በመገንባት ትክክለኛውን መንገድ እንዳያገኙት ማድረግ፤ ከዛም የአንተ ነው ትክክለኛው እንጂ የእነንተና አይደለም እያለ አንዱን በአንዱ ላይ ማነሳሳትና እርስ በእርስ በማፋጀት ግራ ማጋባት የተዋጣ ሥራ ሆኖለታል፡፡ ወገኖቸ ልታውቁት የሚገባው የአዳምንና የልጆቹን ወደ ቀደመው ልዩ መኖሪያ መመለሳቸውን እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ባለብዙ ምህረቱ ጌታ አምላካችን ለእነርሱ ካለው ፍቅር የተነሳ ከእነርሱ በበለጠ ይፈልገዋል፡፡ ስለዚህ አምላካችን ለዚህ አላማ አንድና ብቸኛ የሆነ መንገድ አዘጋጀ፡፡ ሰይጣን እነዛን መንገዶች የሠራው ይህ ብቸኛውና ትክክለኛው መንገድ እንዳይታወቅ ለማድረግ ነው፡፡ አስተዋይ የሆኑና እርሱን የሚፈልጉ፣ ከመንገዶቹ ሁሉ ይህንን መንገድ መለየት ይችላሉ፡፡ በአምላካችን የተዘጋጀልን ትክክለኛ መንገድ እኔ መንገድ ነኝ ያለው ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ እርሱም አምላካችን ወደ አዘጋጀልን የዘለአለም መኖሪያ፣ ወደ ገነት የሚያደርሰን ብቸኛውና አማራጭ የሌለው መንገድ ነው፡፡

<u>**እውነት ነኝ አለ፡-**</u>

መንገድ ብቻ ሳልሆን እርግጠኛ እንድትሆኑ እውነትና እውነተኛ ገነት የማደርስ መንገድ ነኝ አትተራጠሩ አለ፡፡ ወገኖቸ የምታዩአቸው ሃይማኖት የተባሉት መንገዶች በሙሉ የሰው ልጆች ወደሚናፍቁት የዘላለም መኖሪያቸው የሚያደርሱ እውነተኛ መንገዶች አይደሉም፤ ከነዛ መካከል እስልምና አንዱ ነው፤ ሁሉም አድራሻቸው ገሃነም ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን እውነተኛ መንገድ ስለሆነ ወደ ናፍቆታችሁ ወደ ገነት፣ የሚያደርስህ የሚያደርስሽ ከአምላካችን የተሰጠ ልዩና ብቸኛ እውነተኛ

መንገድ ነው፡፡ በዚህ እውተኛ መንገድ ላይ የሚጓዙ ሁሉ በመጨረሻው ዘመን በፍጹም አያፍሩም፡፡ ከኃጢአትና ከዘለአለም ሞት ባርነት ነጻ የሚያወጣ እውነተኛና እውነት የሆነ ብቸኛው መንገድ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህንን እያለ ያለው እንዲሁ አይደለም፤ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲለያዩ ላደረጋቸው ለኃጢአት ትክክለኛ መፍትሔ ይዞ በመምጣቱ እንጂ፡፡

**<u>እኔ ሕይወት ነኝ አለ፡-</u>**

በኃጢአት ምክንያት ከአምላኩ ለተለየው ሰው ወደ ዘለአለም መኖሪያው ለመመለስ የሚያስፈልገው ሕይወት ነበር፡፡ ምክንያቱም አታድርግ የተባለውን ባደረገ ጊዜ ወደ እርሱ የመጣው ሞት ነበርና፤

**ኦሪት ዘፍጥረት** 2 ፡ 16-17

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።

የኃጢአት ደሞዝ ሞት ስለሆነ ሞተ፤ በሌላ አነጋገር ከእግዚአብሔር ክብርና ከሚኖርበት ንጹሕ ሕይወት ተለየ፡፡ ስለዚህ እርሱ ሕይወት ሆኖ ሕይወት ይዞ ወደ እኛ መጣ፡፡

**ወደ ሮሜ ሰዎች** 3 ፡ 22-23

እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤

ደግሞም እንዲህ ይላል፡-

**ወደ ሮሜ ሰዎች** 6 ፡ 23

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።

አዳምና ዘሮቹ ይህንን የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የሆነውን ሕይወት እንደገና መልሰው ማግኘት ካልቻሉ በስተቀር እንደገና ወደ ገነት ተመልሶ መልካሙን የእረፍት ሕይወት መኖር አይችሉም፡፡ በአባታችን በአንዱ በአዳም ኃጢአት ምክንያት በሁላችን ላይ ሞት ነግሷል፤ እርስዎም በዚህ ኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ሕይወት ተለይተው ሞተዋል፡፡ በስጋ

ከሞተ ሰው የሚለዩት ንስሃ ለመግባትና ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ እድል ያለዎት መሆኑ ብቻ ነው፡፡ እንግዲህ በገነት ለዘለአለም በደስታ ለመኖር ዋስትና የሚሆነው የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተልኮለዎታልና ጊዜ ሳያጠፉ ይውሰዱ፡፡

**ወደ ሮሜ ሰዎች 5 ፡ 15**

*ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።*

እግዚአብሔር አምላክ ጻድቅ የሆነ ባህሪው የኃጢአትን መቀጣት እንደሚፈልግ፤ ኃጢአትም መቀጣት እንደሚገባው ሁላችን ይንስማማበት ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ጌታ ኢየሱስ ስለ ኃጢአዎት ሊቀበሉት ይገባ የነበረውን ቅጣትዎትን እርሱ በእርስዎ ፋንታ መስቀል ላይ ተቀብሎለዎታል፤ በእርስዎ ላይ ነድዶ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቁጣ እራሱ ሰለ እርስዎ ተቀብሎት አብርዶለዎታል፡፡ ይህ ነው ፍቅር!

**ትንቢተ ኢሳይያስ 53 ፡ 4-6**

*በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።*

ውድ አንባቢ ስለኃጢአትዎት ሊከፍሉት የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እርስዎን ተክቶ በመሞት ከፍሎለዎታል፤ ደስ ይበልዎት! እራሱን አዋርዶ ወደ ምድር የመጣው ለዚህ ነበር፡፡ አሁን ከእርስዎ የሚጠበቀው ይህንን በመስቀል ላይ የተሰራለዎትን የመዳንዎትን ሥራ በማመንና ኃጢአተኛነዎትን በመናዘዝ፣ የዘለአለምን ሕይወት በነጻ፣ ያለምንም ድካም ለመቀበል መወሰን ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ኃጢአት ባፈሰሰው ደም ስለሚገኘው የኃጢአት ስርየት ሲናገር፡-

**1ኛ የዮሐንስ መልእክት 1 ፡ 7-9**

*ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን*

እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።

ውድ አንባቢ ስለ ኃጢአትዎት ዋጋ ይሆን ዘንድ መስቀል ላይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተሠራለዎትን ሥራ አምነው ቢቀበሉ፣ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ያጡትን የእግዚአብሔርን ሕይወት እንዲሁ በነጻ ይቀበላሉ፤ ለዘለአለምም በሕይወት ከእርሱ ጋር በገነት ይኖራሉ፡፡ የምስክርነቱን ቃል ያንብቡ እንዲህ ይላል፡-

**1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5 ፡ 10-13**

በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል። እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።

እንግዲህ ይህንን የሕይወት መንገድ ቢቀበሉ የገነት ነዋሪ መሆንዎትንና ከሥጋ ሞት በኋላ ወደዛው ለመግባትዎት ገና በምድር ላይ እያሉ ፍጹም እርግጠኛ ይሆናሉ፤ ብቸኛው ወደ ገነት የመግቢያ መንገድ ይህ ብቻ ነው፡፡ አሁን ይህንን የሕይወት ጌታ በማመን ተቀብለው የመንግስተ ሰማይ ወገን ይሆኑ ብዬ እጋብዘዎታለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው በዚህ መንገድ ካልሆነ በቀር ወደ አብና ከእርሱ ጋር ለመኖር ወደ ገነት መጓዝና ወደዛ መግባት አይችሉም፡፡ ዛሬ ወደዚህ ጌታ ሊመጡና ከማንም በላይ ከሚያፈቅርዎት ውድ አምላክዎት ጋር ሊታረቁ ይገባል፡፡ እኔም እባክዎትን ይታረቁ ብየ እንለምንዎታለሁ፡፡ ይህንን የሕይወት መንገድ ለመከተልና በእርሱ ለመኖር ፈቃደኛ ከሆኑ የሚከተለውን ጸሎት ይጸልዩ፡-

- እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ ለእኔ ስላለህ ፍቅር አመሰግናለሁ፤ እንደምትወደኝ አውቄአለሁ
- ስለላክልኝ የሕይወት መልእክተኛ ስለ ልጅህ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ፤
- ጌታ ኢየሱስ ሆይ በእኔ ኃጢአት ምክንያት መስቀል ላይ ሞተህልኛል አምናለሁ፤ ከሞትም መነሳትህንም አምናለሁ
- እኔ ኃጢአተኛ ሰው መሆኔን አምናለሁ፤ አሁን ይቅር እንድትለኝ፣ ከበደልም በፈሰሰው ደምህ አጥበህ እንድታነጻኝ እለምንሀለሁ፤
- ልጅህ አድርገህ ተቀበለኝ፤ ለአንተ ቀሪ ሕይወቴን ለመገዛት ወስኛለሁ፤ ዓለምንና ሥራውን እንዲሁም ሰይጣንን ክጃለሁ፤

- ስለተቀበልከኝ፣ ይቅር ስላልከኝ፣ ልጅህም ስላደረግከኝ አመሰግናለሁ፡፡

እንኳን ደስ ያለዎት! አሁን ይህንን ጸሎት በጸለዩበት ቅጽበት ከዘለአለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት በመሻገር የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን መብት ተቀብለዋል፡፡ ደግሜ እላለሁ እንኳን ደስ ያለዎት! ከዚህ በኋላ የሕይወት ምግብ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ፤ ወደ እውነተኛ ቤተክርስቲያን በመሄድ በዛ ሕብረት ያድርጉ፡፡ ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት አስፈላጊ ነው፡፡ ጌታ በነገር ሁሉ ይባርከዎት!! በአድራሻየም ሊያገኙኝ ይችላሉ፡፡

**<u>ዋቢ መጽሐፍት፡-</u>**


መጽሐፍ ቅዱስ
ሳሂህ አል-ቡኻሪ
ሳሂህ ሙስሊም
ሱና ማሊክ ሙዋታ
ተፍሲር ኢብን ካሲር
ቁርአን
የእስልምና መሰረተ አሳቦች ክፍል ሁለት
Protect Yourself from the jinn and Shaitan, by Wahid Abd Al-salam Bali
Al-hadith Mishkat Masabih volum 2


አስተያየትና ጥያቄ መጠየቅ ለምትፈልጉ ሁሉ የሚከተለውን አድራሻ መጠቀም ትችላላችሁ፤ ፈጥኘ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡

JEA.2001@yahoo.com